www.chilot.me

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ አምስተኛ ዓመት ቁጥር ፵፰
አዲስ አበባ መጋቢት ፳፯ ቀን ፪ሺ፲፩ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

25th Year No.48
ADDIS ABABA 5th April, 2019

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፳፬/፪ሺ፲፩ ዓ.ም

የአፍሪካ አህጉራዊ ነፃ የንግድ ቀጣና ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ ……………………ገጽ ፲፩ሺ፪፻፪

## Content

Proclamation No.1124/2019

Agreement Establishing the African Continental Free Trade Area, Ratification Proclamation …..…………………………...………….Page 11202

## አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፳፬/፪ሺ፲፩

**የአፍሪካ አህጉራዊ ነፃ የንግድ ቀጣና ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ**

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት የአፍሪካ አህጉራዊ ነፃ የንግድ ቀጣና ስምምነትን መጋቢት ፲፪ ቀን ፪ሺ፲ ዓ.ም በሩዋንዳ ኪጋሊ በተደረገው የአፍሪካ ሕብረት ፲ኛው አስቸኳይ የመሪዎች ጉባኤ ላይ የፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት መጋቢት ፲፪ ቀን ፪ሺ፲፩ ዓ.ም ባካሄደው ስብሰባ ያፀደቀው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገመንግስት አንቀፅ ፶፭ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ “የአፍሪካ አህጉራዊ ነፃ የንግድ ቀጣና ስምምነትን ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፳፬/፪ሺ፲፩” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## PROCLAMATION NO. 1124/2019

**A PROCLAMATION TO RATIFY THE AGREEMENT ESTABLISHING THE AFRICAN CONTINENTAL FREE TRADE AREA**

**WHEREAS,** the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia have signed The Agreement Establishing the African Continental Free Trade Area in Rwanda, Kigali, on the 21st day of March, 2018;

**WHEREAS,** the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said Agreement at its session held on the 21st day of March, 2019;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55(1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby Proclaimed as follows;

### 1. Short Title

This Proclamation may be cited as the “Agreement Establishing the African Continental Free Trade Area, Ratification Proclamation No. **1124**/2019.”

www.chilot.me



፪. **ስምምነቱ ስለመፅደቁ**

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት መጋቢት ፲፪ ቀን ፪ሺ፲፰ ዓ.ም በሩዋንዳ ኪጋሊ በተደረገው የአፍሪካ ህብረት ፲ኛው አስቸኳይ የመሪዎች ጉባኤ ላይ የተፈረመው የአፍሪካ አህጉራዊ ነፃ የንግድ ቀጣና ስምምነት ፀድቋል፡፡

፫. **የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ኃላፊነት**

የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ይህንን ስምምነት የማስፈፀም ኃላፊነት በዚህ አዋጅ ተሰጥቶታል፡፡

፬. **አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ መጋቢት ፳፯ ቀን ፪ሺ፲፩ ዓ.ም**

**ሳህለወርቅ ዘውዴ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

2. **Ratification of the Agreement**

The Agreement Establishing the African Continental Free Trade Area, signed in Rwanda, Kigali, on the 21st day of March, 2018, is hereby ratified.

3. **Implementing Organ**

The Ministry of Trade and Industry is hereby empowered to implement the Agreement.

4. **Effective Date**

This Proclamation shall come into force on the date of its publication in the *Federal Negarit Gazette.*

**Done at Addis Ababa on this 5th day of April, 2019.**

**SAHLE-WORK ZEWDE**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**